- **በተቃዋሚ የም/ቤት አባላት ላይ ልዩ ክትትል እንዲደረግ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ለደህንነት ክፍሉ ትዕዛዝ ሰጡ**
- **በም/ቤቱ የተደረጉ ውይይቶች ለሚዲያ ከመቅረባቸው በፊት በካሴት ተቀርፆ እንዲቀርብልኝ ሲሉ መለስ መመሪያ አስተላለፉ**
- **3ቱ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የምርጫ ቦርድን ሐሳብ አንቀበልም በማለታቸው ወያኔ ደነገጠ መግለጫም አወጣ**
- **በናዝሬት ፖሊሶች የሕወሓቶቹን ባለሥልጣናት በጥያቄ አጣደፏቸው**
- **ደብረዘይት የሚገኘው አየር ኃይል ግቢ ውስጥ የውጭ ሐገር ዜጐች ታዩ አማካሪዎች ናቸው ተብሏል፣**
- **ሁለት የማረሚያ ቤት ፖሊሶች ማዕረጋቸውን ተገፈፉ**
- **የወያኔ የፖሊት ቢሮ አባሎች በቤተመንግስት ለ3 ቀናት ድብቅ ስብሰባ አደረጉ**

**ባለፈው ሳምንት የተቃዋሚ ፓርቲዎችና ምርጫ ቦርድ ባደረጉት ውይይት ሳይግባቡ በመቅረታቸው የወያኔውን ቡድን እንዳስደነገጠ ለማወቅ ተችሏል፡፡**

የምርጫ ቦርድ የማሟያ ምርጫ፣ የቀበሌና የወረዳ ምርጫ እንዲደረግ አጭር ቀናት እንሰጣችሁና አቋማችሁን እንድታሳውቁ በማለት ለተቃዋሚ መሪዎቹ ማስፈራሪያ አዘል መልዕክት ቢያስተላልፍም የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎቹ «ይህንን ለመወሰን ጊዜ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ አሁን በቅርቡ አንወስንም፡፡ ይህ ከመሆኑ በፊት ያነሳናቸው ነጥቦች መልስ ሊያገኙ ይገባቸዋል» በማለት የምርጫ ቦርድ ማስፈራሪያን በማጣጣል ሳይስማሙ በመቅረታቸው መለስን ጨምሮ የወያኔ ባለሥልጣናትን ክፉኛ እንዳስቆጣ ለኢህአዴግ ቢሮ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል፡፡

**ቅዳሜ ጥቅምት 16 ቀን 2000 ዓም ከምርጫ ቦርድ ጋር መስማማት እንዳልቻሉና በቀጣይም ድርድር ማድረግ እንደሚፈልጉ የሕብረቱ ሊቀመንበር ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ፣ የቅንጅቱ ሊቀመንበር አቶ ተመስገን ዘውዴ እና የኦፌዴን ሊቀመንበር አቶ ቡልቻ ደመቅሳ በጋራ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ የገለፁ ሲሆን፣ ወደፊትም ምርጫ**

ቦርድን የጠየቅነው ነገር ካልተሟላ በምርጫው ለመሳተፍ እንደሚቸገሩ ይፋ ሲያደርጉ ይህ ድርጊታቸው የወያኔን መሪ መለስን ጨምሮ ቱባ ቱባ ባለሥልጣናትን እንዳበገነ እነዚሁ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል::

እንደ ድፎ ዳቦ ከውጭ እሳት ከውስጥ እሳት የሆነበት የወያኔው ቡድን ታማኝ ተቃዋሚ ናቸው ያላቸውና የም/ቤቱን ሂደት ዴሞክራሲያዊ ነው ለማሰኘት ሲጠቀምባቸው የነበሩት የተቃዋሚ ፓርቲዎች የወሰዱት ድንገተኛ እርምጃ በወያኔ ቡድን በኩል ክፉኛ ድንጋጤን የፈጠረ ከመሆኑም በላይ አስቸኩዋይ መግለጫ ለማውጣት እንደተገደደ ለማወቅ ተችሏል::

እኔ ያልኩት ካልሆነ እያለ ለ16 ዓመታት በግትር አቋሙ ቀጥሎ ያለው ወያኔ ታማኝ ባላቸው ተቃዋሚዎች ላይ ባወጣው በዚሁ መግለጫ ላይ «ምርጫ ቦርድ ያወጣውን መመሪያና ትዕዛዝ ያለመቀበል ማለት ሕገ ወጥነትን ያሳያል:: የዲሞክራሲያዊ መርህን መጣስ ነው» በሚሉና ሌሎች ማስፈራሪያ ቃላቶችን በማከል አትቷል::

ግራ የተጋባው የወያኔ መሪ መለስ ሰሞኑን የተቃዋሚ ፓርቲዎች የወሰዱት አቋም ፍፁም ያልጠበቀውና ያላሰበው በመሆኑ እጅግ ከመበሳጨቱ የተነሳ መለስ ለደህንነቱ አዲስ መመሪያ ማውጣቱን የደህንነት መ/ቤት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጠቁመዋል:: በዚህም መሠረት ይላሉ ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ በዚህም መሠረት «ከጥቅምት 16 ቀን 2000 ዓም ጀምሮ በመላ ሐገሪቱ ውስጥ ያሉ የተቃዋሚ አባሎችና አመራሮች ላይ ከፍተኛ ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግና ሪፖርት እንዲቀርብልኝ» በማለት ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን አብራርተው በተለይም በተወካዮች ም/ቤት ውስጥ የተቀመጡ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችና አባሎች ውሏቸውና ማደሪያቸው አልፎ ተርፎ ከነማን ጋር እንደሚገናኙ ጥብቅ ክትትል እንዲደረግባቸው መመሪያው ከመለስ የወረደ ሲሆን ይህንን የሚፈፅሙ ደግሞ የሕወሓት ደህንነት አባሎች መሆናቸውን ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

ከሐገር ውስጥና ከሐገር ውጭ በተቃውሞና በውጊያ አጣብቂኝ ውስጥ የገባው የወያኔ ቡድን ታማኝ ተቃዋሚ ናቸው ያላቸው አስደንጋጭ እርምጃ ስለወሰዱ ብቻ አቋማቸውን ለማስቀየር ሲል እና የአረመኔነቱን ተግባር ለመውጣት ሲል ለደህንነቱ ክፍል ጥብቅ ቁጥጥር ይደረግባቸው ብሎ መመሪያ ማውረዱ የስርዓቱ ቁንጮዎች እጅግ ከመብገናቸው የተነሳ የሚይዙትንና የሚጨብጡትን እንዳሳጣቸው ለመረዳት ተችሏል ሲሉ ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል::

በተለይም እሁድ ጥቅምት 17 ቀን 2000 ዓም የኢህአዴግ ከፍተኛ ባለሥልጣናት በፓርላማ ግቢ በሚገኘው የኢህአዴግ ቢሮ ውስጥ ዝግ ስብሰባ ያደረጉ ሲሆን፣ በዚሁ ስብሰባ ላይ ቀጣይ መወሰድ ስላለበት እርምጃም የተወያዩበት መሆኑን ለኢህአዴግ ቢሮ ቅርበት ካላቸው ምንጮች ለመረዳት ተችሏል።

እንደ ምንጮቹ ገለፃ ከሆነ በቅርቡ ከተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ጀምሮ እስከ ተራ አባልና ደጋፊ በሚል ሐብታሞችን ጨምሮ የማሰር እርምጃ ሊወሰድ እንደሚችል ያላቸውን ስጋት ገልፀው በተለይም በኦሮሞ ተወላጆች ላይ የተጀመረው የእስራት ዘመቻ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ሳይገልፁ አላለፉም።

አስቂኙና አስገራሚው ነገር ይላሉ የም/ቤት ምንጮቻችን አስቂኙና አስገራሚው ነገር መለስ ዜናዊ የሚይዘውና የሚጨብጠው ነገር ከመጥፋቱ የተነሳ እሱ የሌለበት የተወካዮች ም/ቤት ስብሰባ በካሴት ተቀርፆ እንዲሰጠኝ በማለት ያስተላለፈው ትዕዛዝ ነው ሲሉ ገልፀዋል።

መለስ በንዴትና በብስጭት በየቀኑ የሚያወጣቸው አዳዲስ መመሪያዎች ፈፅሞ ከአንድ መሪ የማይጠበቅ ተራ አንድ ግለሰብ የማይሰራው እጅግ አሳፋሪና አሳዛኝ ተግባር መሆኑንም እነኚሁ ምንጮች ገልፀው የም/ቤቱ ስብሰባ ውሎ በየጊዜው እየተቀረፀ ለሚዲያ ከመላኩ በፊት ለኔ ይሰጠኝ ማለቱ ሰውየው እብደት መጀመሩን ፍንጭ ያሳየ ነው ሲሉ ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል።

<u>በውስጥና በውጭ ግራ የተጋባው መለስ ዜናዊ ሰሞኑን ደግሞ ከጥቅምት 18 ቀን 2000 ዓም ጀምሮ በቤተ መንግስት ውስጥ የኢህአዴግ ፖሊት ቢሮ አባሎችን ሰብስቦ እያነጋገረ መሆኑን የቤተ መንግስት ምንጮቻችን ገልፀዋል።</u>

እንደ ምንጮቹ ገለፃ ከሆነ የወያኔው መሪ መለስ እሱ እራሱ ግራ ገብቶት ሹማምንቱንም ግራ እያጋባቸው እና ስብሰባ ጀምሮ ትቶ እየወጣ እንደገና እየተመለሰ ከሰኞ ጥቅምት 18 ቀን 2000 ዓም እስከ ረቡዕ ጥቅምት 21 ቀን 2000 ዓም ድረስ ምስጢራዊ ስብሰባ ቀጥሎ እንደነበረ አውስተው በተለይም መለስ ከመቼውም ጊዜ በላይ የመረጋጋት ስሜት ፈፅሞ የማይታይበት ከመሆኑም በላይ የተሰበሰቡትን የፖሊት ቢሮ አባል ተብዬዎች ስም እየጠራ ይሰድባቸው እንደነበረም ምንጮቹ አጋልጠዋል።

ሲያልቅ አያምር እንዲሉ ወያኔና የወያኔ ሹማምንቶች ዛሬ በሐገሪቱ ውስጥ እና ከሐገር ውጭ በተከሰተው የፖለቲካ እና የማህበራዊ ቀውስጥ ሳቢያ መላወሻ አጥተው እርስ በራስ እንደውሻ እየተናከሱ ነው ያሉት ምንጮች ለተከታተይ 3 ቀናት የፈጀው ምስጢራዊ ስብሰባ ምን እንደሆነ ባይታወቅም ሁሉም አባሎች ግን በስብሰባው ላይ ሲጯጯሁ እንደሚውሉ ሳይጠቅሱ አላለፉም።

ለወትሮው ለስላሳና ቡና የሚያቀርቡ መደበኛ ሰዎች የነበሩ ሲሆን በነዚህ 3 ቀናት ስብሰባ ወቅት ግን ሌሎች አስተናጋጆች ተቀይረው መሥራታቸውን የጠቆሙት ምንጮች ይህ የሚያስረዳው የስብሰባ ክባድነት እና ምስጢሩ ሾልኮ እንዳይወጣ ከማድረግ አኳዋያ መሆኑንም አስረድተዋል።

የመለስ ቡድን ግራ ተጋብቶ ባለበት በዚህ ወቅት የፌዴራል ፖሊስ የሕወሓት ከፍተኛ ባለሥልጣናት ለክልሉ ፖሊሶች የማሻሻያ ኮርስ እንሰጣለን በሚል በአሙዲአስ የተባለ ለወያኔ ቅርበት ያለው ግብረሰናይ ድርጅት አዘጋጅነት የተጀመረ ሲሆን፣ ስሞኑን ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ በናዝሬት 3 ቀን የፈጀ ንትርክ የሞላበት ውይይት መደረጉ ታውቋል።

ከአርብ ጥቅምት 15 ቀን 2000 ዓም ጀምሮ እስከ እሁድ ጥቅምት 17 ቀን 2000 ዓም ድረስ ለ3 ተከታታይ ቀናት ሲካሄድ በሰነበተው ትምህርታዊ ስብሰባ ላይ የኦሮሚያ ፖሊሶች ስልጠናውን ይሰጣሉ ለተባሉት የሕወሓት ቱባ የፖሊስ ባለሥልጣናት ላይ የጥያቄ ውርጅብኝ እንደ ዶፍ በማዝነባቸው ክፉኛ ተደናግጠው እንደነበርና በተለይም አሁን ያለውን የሐገሪቱን የአንድ ብሔር የበላይነት መዋቅር በፅኑ እንደሚቃወሙ ጨምረው በመግለፃቸው እጅግ ያልጠበቁት ዱብ እዳ እንደሆነባቸው ለማወቅ ተችሏል።

«እስከ ዛሬ ድረስ እናንተ በምትሰጡት መመሪያና ትዕዛዝ የገዛ ወገናችንን ስንጨፈጭፍ ኖረናል። ከሕዝባችን ጋርም እንድንቃቃር አድርጋችሁናል። ከዚህ በኋላ ግን በሕግ ሽፋን ስም የትምስጡትን ሕዝብን ግደሉ የሚል መመሪያ ፈፅሞ ተግባራዊ አናደርግም» ሲሉ በፅናት ሲቃወሙ እንደነበርም ለማወቅ ተችሏል።

በተለይም «የኦሮሞ ሕዝብ ብዙ ነው ሐገሪቱም ሰፊ ናት እናንተ ከላይ እስከታች ድረስ ስልጣኑን ተቆጣጥራችሁ የያዛችሁት በምን መስፈርት ነው?» የሚል ጥያቄ ከአንድ የኦሮሚያ ክልል ፖሊስ ሲነሳ በአዳራሹ ውስጥ የነበሩ ተሰብሳቢ ፖሊሶች

በጭብጨባ አራዳሹን ሲያናጉት ስልጠና እንሰጣለን በማለት በመድረኩ ላይ የነበሩት የሕወሓቶች ባለሥልጣናት እጅግ ተስፋ ከመቁረጣቸውም በላይ መልስ ለመስጠት ተቸግረው እንደነበረም ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ያስረዳል።

በወቅቱ ሥልጠና ይሰጣሉ ከተባሉት አንደኛው ባለሥልጣን «እኛ ዝርዝር ውስጥ መግባት አንሻም። ይሁን እንጂ እኛ በሐገሪቱ ውስጥ ያለውን መዋቅር የሰሩትን ሰዎች አናውቅም» በማለት ሰንካላ ምክንያት የሰጠ ሲሆን በስልጠናው ላይ ተካፋይ የነበሩት ፖሊሶች ግን ይህ ሊዋጥላቸው እንዳልቻለም ከገለፃቸው ለማወቅ ተችሏል።

ወያኔ በመሐል ሐገር አስፍሮት የነበረውን ጦር ወደ ግንባር ለቅሞ የወሰደ በመሆኑ በምትኩ በፌዴራል ፖሊስ ብቻ መላ ሐገሪቱን ለመቆጣጠር ስለማይችል በክልል ፖሊሶች ጥበቃውን ሊያጠናክርና «እሰረው፣ ግደለው» የሚለውን የነመለስን መመሪያ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ቀድመ ዝግጅት ለማድረግ ፖሊሶችን ማስተማር የሚያስፈልግ በመሆኑ ይህንን ስልጠና ለመስጠት ቢጓዙም ያገኙት ምላሽ አስደንጋጭ መሆኑን የስልጠናው ተካፋይ ለተዘዋዋሪ ዘጋባቢያችን ገልጿል።

<u>በሌላ በኩል ሻዕቢያና ወያኔ በፈጠሩት ችግር ምክንያት እርስ በእርስ ሲወራረፉ ስንብተው ካለፈው ሳምንት ጀምሮ በቀላል መሣሪያ የተኩስ ልውውጥ ጀምረው እንደነበረ እና ሰሞኑን ደግሞ በቢኤም ከባድ መሣሪያ ልውውጥ መጀመራቸውን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ።</u>

ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ጀምሮ የከባድ መሣሪያ ልውውጥ የጀመሩ ሲሆን ሁለቱ ሐገራት ዋናውን ጦርነት ከመጀመራቸው አስቀድሞ የፍተሻና የኃይል አቅማመጥ የቦታ አያያዝን የሚፈታተሹበት ተኩስ መጀመራቸውን ምንጮቹ ገልፀው የሻዕቢያ ጦር የሠላም ቀጠናውን ጥሶ ወደ ድንበር እየተጠጋ ሲሆን፣ ወያኔም በተለያዩ ቦታዎች ጦሩን ከመቼውም ጊዜ በላይ በትጥቅና በስንቅ እያሟላና እያደራጀ አልፎ ተርፎም ወደ ግንባር እየላከ መሆኑን ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል።

በሁለቱ ቡድኖች መካከል በ1992 ዓም በተደረገው ውጊያ ከ100ሺ በላይ ዜጎች ያለቁበትን ጦርነት ያካሄዱ ቢሆንም ዘንድሮም ከዚያን ጊዜው በከፋ መልኩ በሁለቱም በኩል ከፍተኛ የጦርነት ዝግጅት ሲያደርጉ መሰንበታቸውን ጦርነቱ ቢጀመር እጅግ የከፋ እልቂት ሊከሰት እንደሚችል ከወዲሁ ከፍተኛ ስጋት እንዳሳደረም ምንጮች ገልፀዋል።

ሻዕቢያ ወጣቱን በደርግ ወቅት እንደ ብሔራዊ ውትድርና በግዳጅ ወደ ሳዋ አስገብቶ መሉ የውትድርና ትምህርት ከሰጠ በኋላ ባስፈለገው ጊዜ ጦርነት ለመጥራት አዘጋጅቶት የነበረውን ኃይል በአሁኑ ሰዓት ሰብስቦ በሁሉም ግንባሮች ያሰለፈው ሲሆን፣ ወያኔ በበኩሉ ከ1997 ዓም በሐገሪቱ ምርጫ ተሸንፎ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ በጦሩ መሀል የተቃዋሚ ደጋፊዎች ናችሁ በማለት የካበተ ልምድና እውቀት ያላቸውን ነባር የጦሩን አባላት ካባረረና ከፊሉንም ካሰረ በኋላ በሁሉም ወታደራዊ ማሰልጠኛ ዎች አዲስ ምልምል ጦር አስገብቶ ካሰለጠነ በኋላ ዘንድሮ ለአይቀሬው ጦርነት ለመማገድ ከየካምፑ አውጥቶ ወደ ግንባር እንደላካቸው የመከላከያ ምንጮች ገልፀው በተለይም ከየቀበሌ ገበሬ ማህበሩ የተጠባባቂ ጦር በሚል በግዳጅ ተመልምለውና ሰልጥነው ወደየቤታቸው የተመለሱትንም በማሰባሰብ ወደ የጦር ግንባሩ ልኳል ብለዋል::

በእግረኛው ጦር በኩል ይህን መሰል ዝግጅት ሲያደርጉ የሰነበቱት ወያኔና ሻዕቢያ በአየር ኃይሉም ረገድ እንዲሁ ከፍተኛ ዝግጅት ማድረጋቸውን የመከላከያ ምንጮች ገልፀው በተለይም ሻዕቢያ በዚህ በኩል በ1992 ዓም ከፍተኛ ሽንፈትና ውርደት ያጋጠመው በአየር ጥቃት እንደነበረና አሁን ይህን ቂም ለመወጣት ዝግጅቱን አጠናክሮ የቀጠለ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀው ወያኔ ግን በሚያራምደው ተልካሻ ፖለቲካ እና የአንድ ወገን የበላይነት የተነሳ ነባርና የካበተ እውቀት ያላቸው የቀድሞ የአየር ኃይል መኮንኖች ባገኙት አጋጣሚዎች ሁሉ ሐገር ጥለው እየኮበለሉና እየተሰደዱ ተመናምነው ያሉበት ደረጃ በመሆኑ በቅርቡ ውስጡን ለማደራጀት አስቦ የውጭ ሐገር ዜጐችን በአማካሪነት በሚል በርካታ መኮንኖችን ያስመጣ መሆኑን የአየር ምንጮቻችን ገልፀዋል::

በአሁን ሰዓት የወያኔው ቡድን በሻዕቢያ ላይ ጥቃት ለመሰንዘር ያመቸኛል በሚል ዋናውን የአየር ኃይል ማዘዣ መቀሌ ላይ ሁለተኛውን ባህርዳር ሶስተኛውን እና ድጋፍ ሰጪ ደብረዘይትና አራተኛውን ድሬዳዋ አድርጐ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀው በቅርቡ ከውጭ መጡ የተባሉትም የውጭ ሐገር ሰዎች ወደ ባህርዳርና መቀሌ መጓዛቸውንም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

ዛሬ በሁለቱም ሐገሮች ውስጥ ያሉ ሕዝቦች የኑሮ ውድነቱ እጅግ ከፍተኛ ጫና ፈጥሮባቸው ባለበት በዚህ ወቅት ሁለቱ ቡድኖች በፈጠሩት አለመግባባት የተነሳ ከአቅማቸው በላይ ከፍተኛ ገንዘብ ለጦርነቱ በመመደብ ለከፋ ጦርነት ዝግጅት ማድረጋቸው በእጅጉ አሳዛኝ ከመሆኑም በላይ ለሕዝባቸው ቅንጣት ታክል የማያስቡ ቡድኖች መሆናቸውን ያሳያል ያሉት አንድ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ

የቀድሞ ጦር ከፍተኛ መኮንን የአሁኑ ጦርነት ከተጀመረ ከመቼውም ጊዜ በላይ እልቂትና የኢኮኖሚ ድቀት የሚያስከትል ነው:: ይህንን አስከፊና ዘግናኝ ጦርነት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚመለከተው ስላልሆነ ወያኔ እራሱ እንደጀመረ እራሱ መጨረስ አለበት ሲሉም አስተያየታቸውን ሰጥተዋል::

በሐገሪቱ የተደረጉት ጥናታዊ ዘገባዎች እንደሚጠቁሙት ከሆነ ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝቦች በወያኔው ቡድን ክፉኛ የተጐዱ በመሆናቸው የተነሳ ጦርነቱ የሁለት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በመሆኑ የማይመለከታቸውና እንደውም ለዚህ ጦርነት ቦታ እንደማይሰጡት ገልፀው ድጋፍም ፈፅሞ እንደማያደርጉ ያመለክታል::

በተያያዘ የሰሜን እዝ አካል የሆነው 19ኛ ክ/ጦር ሰሞኑን የማዕረግ እድገት መስጠቱን ይፋ አደረገ:: በሕወሓቱ ጄኔራል ሳዕረ መኮንን የሚመራው ይህ እዝ ለብዙ የጦር ክፍሎች የማዕረግ እድገት የሰጠ ሲሆን በተመሳሳይ ለዚሁ የ19ኛ ክ/ጦር አባሎች ከኮሎኔል እስከ ምክትል አስር አለቃ ድረስ የማዕረግ እድገት የሰጠ ሲሆን በዚህ ወቅት ጦሩ የታጠቃቸውን ከባድ መሳሪያዎችን ለእይታ ማቅረቡንም የመከላከያ ምንጮች ገልፀዋል:: እንደመከላከያ ምንጮች ገለፃ ከሆነ በዚህ ጦር ውስጥ ቢ ኤም 21፣ መድፍ፣ ታንክ፣ አየር መቃወሚያ፣ ባዙቃ ወይም ሞርተር፣ መትረየስ እና ስናይፐር የተባሉ የጦር ሜዳ መሣሪያዎችን ለእይታ ያበቃ መሆኑን ገልፀው ይህ የተደረገበት ዋነኛው ለሻዕቢያ ማስፈራሪያ ይሆናል በሚል ታስቦ መሆኑንም ምንጮቹ ገልፀዋል::

አንቺው ታመጪው አንቺው ታሮጩው እንዲሉ ወያኔ ይጠቅሙኛል ብሎ ያመነባቸውን ያልተማሩና ምንም እውቀት የሌላቸውን የሕወሓት ታጋዮችን የማዕረግ እድገት እየሰጠ ሲያስደስት በአንፃሩ ግን ነባርና በትምህርት የካበተ ልምድ ያላቸውን የቀድሞ ጦር በዚህ እድል ተጠቃሚ ያላደረጋቸው ከመሆኑም በላይ ለተወሰኑት የማዕረግ እድገት የሰጣቸው ቢሆንም በሰበብ አስባቡ መልሶ እየነጠቃቸው መሆኑን ከተለያዩ አካባቢዎች የሚደርሱን ዘገባዎች ያስረዳሉ::

በቅርቡ ለማረሚያ ቤቶች ፖሊሶች ከብ/ጄ/ልነት እስከ ምክትል አስር አለቃነት ድረስ ማዕረግ የሰጠ መሆኑን የገለፅን ቢሆንም «ማዕረግ አሰጣጡ እኛን ያገለለና ከሰራንባቸው ዓመታቶች እና ካለን እውቀት አንፃር ያንሰናል» በማለት ቅሬታ ያቀረቡ የፖሊስ አባሎች ላይ እንደገና ማዕረግ ነጠቃ እያካሄዱ መሆኑን የማረሚያ ቤቶች የውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን ገልፀዋል::

እንደምንጮቹ ገለፃ ከሆነ «ሰሞኑን ማዕረግ አሰጣጡ አድሏዊነት የታየበት ነው እውቀት፣ ልምድና የአገልግሎት ጊዜ ያልተካተተ በመሆኑ ይታይልን» ብለው ያመለከቱ ሁለት መቶ አለቃ ማዕረግ ያላቸውን ጥያቄውን ማቅረባቸው ብቻ እንደ ወንጀል ተቆጥሮ የመኮንነት ማዕረግ ተነፍገው ሃምሣ አለቃ እንዲሆኑ ተደርገዋል ካሉ በኋላ አሁንም በቀጣይነት ጥያቄ ያቀረቡት በሙሉ እየተገፉፉ የጨርቅ ማዕረግ ወይም የበታች ሹም ሊሆኑ እንደሚችሉ ምንጮች ያላቸውን ጥርጣሬ አክለው ገልፀዋል::

በፌዴራል ወህኒ ቤቶች ስር ያሉ አራት ሲሆኑ እነሱም ቃሊቲ፣ ድሬዳዋ፣ ሸዋሮቢትና ዝዋይ ሲሆኑ ሰሞኑን የሚሊኒየም በዓልን እና የማዕረግ አሰጣጡን አስመልክቶ የፖሊስ ባንድ በዝዋይ እስር ቤት ዝግጅት አድርጎ መመለሱንና በቀጣይም ሸዋሮቢት እንደሚያካሂዱ የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ ገልፆ በሁሉም ቦታ ላይ የተሰጠው ማእረግ የአንድ ወገንን የበላይነት ያንፀባረቀ በመሆኑ የወህኒ ቤት ፖሊሶች በዝግጅቱ ደስተኛ ካለመሆናቸውም በተጨማሪ በስርዓቱ ላይ ከፍተኛ ጥላቻቸውን በተዘዋዋሪም ሆነ ቀጥተኛ በሆነ መልኩ እየገለፁ ይገኛሉ በማለት ምንጮቹ ገልፀዋል::

በተለይም ሰሞኑን የወያኔ ቡድንን የሱማሊያ ጉዳይ እያመሳቸው መላወሻ አሳጥቷቸው ስዩም መስፍን አንዴ ባይደዋ አንዴ አዲስ አበባ እያለ ቢንከራተትም አንዳችም ውጤት ያላመጣ በመሆኑ መለስና ጃሌዎቹ ቆሽታቸው እያረረ «ሱማሊያ በዴሞክራሲ መንገድ ሹም ሽረት አደረገች» እያሉ መግለጫ መስጠታቸው እራሳቸውንና መሠሎቻቸውን ብቻ እያታለሉ መሆኑን የአለም ሕዝብ ሳይቀር የተረዳው ነገር ነው ያሉት አንድ የአፍሪካ ሕብረት ዲፕሎማቲክ ምንጭ ከእንግዲህ ወዲያ በሱማሊያ ሠላም አሰፍናለሁ ብሎ መውተርተር ከንቱ ድካም ነው ሲሉም ገልፀዋል::

አክለውም በናይሮቢ ላይ በአሜሪካና መለስ ግፊት የዚያድባሬ መንግስት ወታደር የነበረውን ኮ/ል አብዱላሂ ዩሱፍን ያለምንም ሕዝብ ድጋፍ ሥልጣን ላይ ቢያስቀምጡም ጥቂት እንኳዋን ሳይቆይ እራሱ የሾማቸው ሚኒስትሮች እየከዱ ሐገር ጥለው ከመውጣታቸውም ሌላ ሰሞኑን ስራውን ሲያንቀሳቅስለት የነበረውና የብዙሃን ጉሣ ተወላጅ የነበረውን ጠ/ሚ/ር አሊ ጊዴን እንደገና ከእነ መለስ በተሰጠው ትዕዛዝ ማባረሩ ሱማሊያ ከድጡ ወደ ማጡ እየተነከረች መሆኗን ያሳያል ካሉ በኋላ ለዚህ ሁሉ ወድቀትና ኪሣራ እነ መለስ ተጠያቂ መሆናቸው አይቀሬ ነው ብለዋል::

ጠ/ሚ/ር አሊ ጌዲ እና ፕ/ቱ አብዱላሂ ዩሱፍ ከጥቂት ጊዜ በፊት በሁለቱ መካከል መግባባት ጠፍቶ ንትርክ ውስጥ ገብተው እንደነበርና ይህንኑ ሽኩቻ የወያኔ ቡድን ለመፍታት ጥረት ቢያደርግም ችግሩን ሊቀርፍ ባለመቻሉ ስዩም መስፍን የአለቃውን የመለስን ትዕዛዝ ይዞ ሱማሊያ ሄዶ ጠ/ሚ/ር አሊ ጌዲን ጠርቶ እንደመጣና አሊ ጌዲንም «ስልጣንህን በገዛ ራስህ ጊዜ እንደለቀቅክ ይፋ አድርግ ይህን ካላደረግክ የከፋ ችግር ውስጥ ትገባለህ» በማለት በሁለት ተከታታይ ቀናት በቤተ መንግስት ውስጥ የቁምእስረኛ አድርገውት እንደነበረ እነዚሁ የዲፕሎማቲክ ምንጮች ገልፀው በዚያን ወቅት አሊ ጌዲ ስልጣኑን እንደሚለቅ ለነመለስ ነግሯቸው እንደነበረም መቀመጫቸው አዲስ አበባ የሆኑ የተለያዩ ሐገራት አምባሳደሮች ሰምተው፣ ተገርመው እንደነበርና ዛሬ ያን ጊዜ የተሰራውን በተግባር ሆኖ ማየታቸው በመለስና ጃሌዎቹ እየተሰራ ያለውን ሁኔታ በግልፅ መረዳታቸውን ምንጮቹ አብራርተዋል::

በሱማሊያ ትልቁ ጉሣ የሚባለው የሐውዬ ጉሳ ተወላጁ አሊ ጌዲ እንደ አለቀ እቃ ተወርውሮ ለጊዜው ለ30 ቀናት ያህል ቋሚ ጠ/ሚ/ር እስከሚሾም ድረስ ፕሬፊሰር ሳሊም ኢብሮው የተባለ የዩኒቨርስቲ መምህር የተቀመጠ ሲሆን፣ ይህ ሹም ሽረት በባይደዋ እየተካሄደ ባለበት ወቅት በሞቃዲሾ የወያኔ ወታደሮች እና የእስልምና አክራሪው ቡድን በከባድ መሣሪያ እየተጨፋጨፉ መሆኑን አለም አቀፍ ሚዲያዎች ገልፀዋል::

በሱማሊያ ሞቃዲሾ የገባው የወያኔ ወታደር በቀየኑ እንደቅጠል እየረገፈ መውጫ ቀዳዳ ጠፍቶት ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሕይወቱን ለማትረፍ ቢሯሯጥም ሊሳካለት ያልቻለ መሆኑን የተገነዘቡ አንድ የቀድሞ ከፍተኛ ማዕረግ ያላቸው መኮንን ጦሩ ተባብሮ እንድ ጊዜ በርግዶ ሞቃዲሾን ጥሎ መውጣት እና እራሱን ማትረፍ ካልቻለ አሁን ባለው ሁኔታ ከቀጠለ ለወሬ ነጋሪ አንድም የሚተርፍ አይገኝም ሲሉ ያላቸውን ስጋትና መደረግ ያለበትን ምክር ለግሰዋል::

አሁን ሰሞኑንም የወያኔው ቱባ ባለሥልጣን ስዩም መስፍን እንደ ውሃ ቀጅ አንዴ ባይደዋ አንዴ አዲስ አበባ በኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረትና ሐብት በሆነው ቦይንግ አውሮፕላን እየተመላለሰ የውስጥ ችግራቸውን መፍታት ያቃታቸው ወያኔዎች የራሷ እያረረባት የሰው ታማስላለች እንዲሉ በሱማልያ ወስጥ እጃቸውን አስገብተው እየዳከሩ መገኘታቸው አስገራሚ ከመሆኑም በላይ በሕዝብና ሐገር ሐብት ላይ መቀላዳቸው እጅግ የሚያንገበግብ ነው ሲሉ እኚሁ የቀድሞው የጦር መኮንን እልህና ቁጭት በተቀላቀለበት ስሜት ለተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን አስተያየት ሰጥተዋል::